# አለም አቀፍ የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች (IPSAS) ትግበራ

*በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት*

የኢፌዲሪ መንግስት ተጠያቂነትን፣ ግልጸኝነትን እና መልካም የመንግስት ሃብት አስተዳደርን ለማስፈን ሲተገብራቸው ካቀዳቸው ሪፎርሞች አንዱ የመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓትን ማዘመን ነው።

ለዚህም አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለውን የአለም አቀፍ የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች (IPSAS) ለመተግበር በዝግጅት ላይ ይገኛል። ስለሆነም ትግበራውን በበላይነት የሚቆጣጠር በከፍተኛ የመንግስት ሃላፊዎች የተዋቀረ ስቲሪንግ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ስራ ተገብቷል።

## 🌍 IPSAS ምንድን ነው?

IPSAS ለመንግስት ሂሳብ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኘ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች ስብስብ ሲሆን በአክሩዋል የሂሳብ አያያዝ (ማለትም ገንዘብ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ግብይቶች ሲከሰቱ በመመዝገብ) ላይ የተመሰረተ ነው፡

እነዚህን ደረጃዎች የሚያወጣውም ሆነ የሚያሻሽላቸው IPSAS ቦርድ የተባለ በአለም አቀፉ የአካውንታቶች ፌዴሬሽን ስር ያለ ገለልተኛ የመንግስት ሂሳብ ባለሙያዎች ስብስብ ነው።

## ✅ IPSAS ለምን?

የIPSAS በመንግስት ደረጃ መተግበር የሚከተሉትን ጥቅሞች ያመጣል፡

- 🔍 **ለተሻለ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት፡-** የመንግስትን የፋይናንስ ሁኔታ እና አፈጻጸም ሙሉ በሙሉ ግልጽ በሆነ መልኩ በማቅረብ የህዝብ ሃብት አጠቃቀም ቁጥጥርን እና ተጠያቂነትን ያሳልጣል።
- 📊 **የመንግስትን የፋይናንስ አቅም በትክክል ለማሳየት:** የሂሳብ ረፖርት አዘገጃጀት ወጥነት ያለው እንዲሆን በማድረግ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ያካተተ የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት የመንግስትን የፋይናንስ ሁናቴ በትክክል ለማሳውቅ ያስችላል፣
- 💼 **የተሻለ ውሳኔ ለመስጠት፡-** አስተማማኝና ተገቢ የሆነ የፋይናንስ መረጃ በመስጠት በመረጃ ላይ የተመሰረተ የፖሊሲ ቀረጻና፣የሃብት ክፍፍል ውሳኔዎችን ለመወሰን ይረዳል፣
- 🏦 **ወጪ ቆጣቢ የገንዘብ ምንጮችን ለማሳደግ፡-** የሃገሪቱን የፋይናንስ ሪፖርት ከዓለም አቀፍ ምርጥ ልምዶች ጋር በማጣጣም በአበዳሪዎች፣ ኢንቨስተሮች እና ሌሎች ዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች ዘንድ ያለውን ተዓማኒነት ያሳድጋል።
- ⚖️ **ለተሻለ የፋይናንስ አስተዳደር፡-** የመንግስት ንብረቶችን እና እዳዎችን ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተዳደር ይረዳል።
- 🌐 **ለተሻለ ንጽጽር፡** የመንግስት የሂሳብ ሪፖርቶች ከሌሎች ሃገራት ረፖርቶች ጋር በቀላሉ የሚነጻጸሩ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ በመሆኑም የዓለም አቀፍ እርዳታ ሰጪ አካላት ፍላጎትን በቀላሉ የሚያሟላ ይሆናል፣

## 🤝 የባለድርሻ አካላት ሚና

***ገንዘብ ሚኒስቴር***

- *IPSAS እንዲተገበር ሕግና ፖሊሲ ማዘጋጀት*
- *የመንግስት የሂሳብ ሪፖርትን ግልጽ ማድረግ*
- *ሰው ኃይልንና ስልጠናን ማዘጋጀት።*
- *ትግበራውን በበላይነት መከታተል*

***ፓርላማ***

- *በIPSAS ላይ የተመሠረተ የመንግስት የሂሳብ ሪፖርት እንዲቀርብ እና እንዲጠበቅ ክትትል ማድረግ።*

***ኦዲተሮች***

- *የIPSAS ትግበራ ትክክለኛ እንዲሆን ኦዲት ማድረግ።*
- *የመንግስት ፋይናንስ መግለጫ ከደረጃዎቹ ጋር እንደሚዛመድ ማረጋገጥ።*

***የመንግስት ሰራተኞች***

- *የሂሳብ መዝገቦችን በIPSAS መሰረት ማዘጋጀት።*
- *እውነተኛ እና ታመኝ የፋይናንስ መረጃ ማቅረብ።*

***ዜጎች***

- *የመንግስት የፋይናንስ ሪፖርትን መጠየቅ እና መጠቀም*

***ዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች (IMF, World Bank, Donors)***

- *የIPSAS ማስፈጸምን በቴክኒክና በፋይናንስ ድጋፍ ማድረግ።*
- *የሌሎች ሃገራት ተሞክሮችን ማግኘት እንዲቻል ማገዝ*

***IPSAS ለተሻለ የሕዝብ ሃብት አስተዳደር***

***በገንዘብ ሚኒስቴር የመንግስት ሂሳብ ዲቪዥን***